በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትሕ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ማ ርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/1028/18

ቀን 24/04/2018 ዓ/ም

ለአብክመ ስራና ክሕሎት ቢሮ

ባህር ዳር፤

ጉዳዩ፡ መመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው በመላክ እንዲሁም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አዋጁ በወጣ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል።

በዚህ መሰረት የአብክመ ስራና ክሕሎት ቢሮ በቁጥር ስ/ስ/ም/ቢ/ሃ/02/85/371 በቀን 30/01/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የወጣቶችን ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማስተዳደር የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 51/2014 ዓ/ም ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወሳል።

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ቁጥር 51/2014 ዓ/ም ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮና አስተካክሎ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 30/2018 ዓ.ም አድርጎ የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ 16 ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

ይስማው ዘመነ

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት
የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤(ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

ፍትህ ቢሮ

## መመሪያ ቁጥር 30/2018 ዓ/ም

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የወጣቶችን ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማስተዳደር የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት የአፈጻጸም መመሪያ

በክልላችን የወጣቶችን ተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር አቅርቦት ለማመቻቸት በፌደራል መንግሥቱ ከፍተኛ ገንዘብ ተመድቦ በርካታ ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም የክልሉን ወጣቶች ተጠቃሚ ማድረግ ቢቻልም በየደረጃው የብድር ማስመለስ ተገቢውን ትኩረት ተሰጥቶት ባለመሠራቱ ምክንያት ተጨማሪ የብድር አገልግሎት ለማቅረብ እክል የፈጠረ በመሆኑ፤

በ2009 ዓ.ም በፌደራል መንግሥት የተሰጠውን የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር ለማስተዳደር ከአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ጋር የተወሰደ የኮሚሽን የውል ስምምነት አሁን ተቋሙ ወደ ባንክ በማደጉ ስምምነቱን የፈጸመው ተቋም የስም፣ የተቋማዊ ቁመና ለውጥ ያደረገ ስለሆነና የፈንዱን አስተዳደር ከአብቁተ ወደ ጸደይ ባንክ በማስተላለፍ የኮሚሽን አስተዳደር ስምምነቱን ማደስ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከዚህ በፊት በነበረው የአሠራር ሥርዓት የተሰራጨውን ብድር ለማስመለስ ተገቢውን ትኩረት ባለመሰጠቱና እንዲመለስ ባለመደረጉ የብድር ማስመለስ ምጣኔው ከሚጠበቀው በታች በመውረዱ በቀጣይነት የብድር ስርጭት ሂደትን የገደበው በመሆኑ የሥራ እድል ፈጠራ ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በማሳደሩ በቀጣይነት የብድር ማስመለስ ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጠው ለማድረግ፤

የነበረው የብድር አስተዳደር ሥርዓት በወረዳ ደረጃ የብድር ማስመለስ ምጣኔ ከ97 በመቶ በታች ከሆነ የብድር አገልግሎት መስጠት እንደማይቻል ማስቀመጡ ለብድር ስርጭት ሂደቱ ገዳቢ በመሆኑ ገደቡን ለማንሳት፤

ከዚህ በፊት በተዘዋዋሪ ብድር ድጋፍና በራሳቸው ወይም በቤተሰቦቻቸው ደጋፊነት ወደ ሥራ የገቡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ያለባቸውን የገንዘብ ችግር በመፍታት ተጨማሪ የሥራ እድል እንዲፈጥሩ ለማስቻል የተዘዋዋሪ ብድር ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አሠራር ለመዘርጋት፤

የተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር ስርጭት በተለይ ከዋስትና ጋር ተያይዞ የነበሩ የአሠራር ክፍተቶችን ለመሙላት፣ የከተማ ወይም ወረዳ አስተዳደር በማይመለስ ብድር ተጨማሪ ኃላፊነት እንዲወስድ ለማድረግ፤

የብድር ተመላሽ ከ97% እና በላይ ካልሆነ ብድር ማሰራጨት እንደማይቻል የተገደበ ሲሆን የአመላለስ ምጣኔው ደግሞ ከ97% በታች በመውረዱ በተለያዩ ጊዚያት ተመልሶ የተቀመጠውን ገንዘብ አለመጠቀሙ በኢንተርፕራይዝ ልማትና በሥራ ዕድል ፈጠራ ተግባራት አፈፃፀም ላይ የራሱን አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ የሚገኝ በመሆኑ፤

በዚህ የተነሳ መሥራት ለሚችሉ ወጣት ሥራ ፈላጊዎች ወይም ሥራ ፈጣሪዎች የሥራ እድል ተጠቃሚ ወይም ሥራ እንዲፈጥሩ ማድረግ ባለመቻሉ ይህንን ችግር መፍታት ጊዜው የሚጠይቀው ኃላፊነት በመሆኑ፤

በብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ "የወጣቶችን ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ ቁጥር 30/2018 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1/ "ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሥራና ስልጠና ቢሮ ሲሆን በስሩ ያሉትን መዋቅሮችም ያጠቃልላል፤

2/ "ባንክ" ማለት ከዚህ በፊት የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም በሚል ፍቃድ ሥራ ላይ የነበረው የፋይናንስ ተቋም ሲሆን በክልሉ በሁሉም አካባቢ የነበሩትን ቅርንጫፎችና ሳተላይቶች በመያዝ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የባንክነት ፍቃድ በማግኘት ሥራ ላይ ያለውና የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ብድርን ለማስተዳደር ከአብቁተ ጋር የተወሰደውን የውል ወይም የኮሚሽን ስምምነት ይዞ የቀጠለው ጸደይ ባንክ ነው፤



ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice

3/ "የአንድ ማዕከል አገልግሎት" ማለት በከተሞች የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ሕጋዊ ለማድረግና መንግሥታዊ አገልግሎቶችን በተቀናጀ መልኩ በአንድ ስፍራ እንዲያገኙ ለማድረግ የተቋቋመ መንግሥታዊ ተቋም ወይም አደረጃጀት ነው፤

4/ "ቀበሌ" ማለት በገጠር ወረዳ ስር የሚገኝ ወይም የአንድ ማዕከል ባልተቋቋመበት ከተማ ውስጥ የሚገኝ ቀበሌ ነው፤

5/ "አዲስ ኢንተርፕራይዝ" ማለት በኢንተርፕራይዞች አደረጃጀት መሠረት ሕጋዊ ፍቃድ የሚያገኝና ፍቃዱን አግኝቶ ወደ ሥራ ከተሰማራ አንድ ዓመት ያልሞላው ሲሆን ሲቋቋም የተሟላ ወይም በከፊል የመንግሥት ድጋፍ አገልግሎት ያገኘ ነው።

6/ "ነባር ኢንተርፕራይዝ" ማለት በኢንተርፕራይዞች አደረጃጀት መሠረት ሕጋዊ ሰውነት ወይም ፍቃድ አግኝቶ አንድ ዓመትና በላይ የሆነው ሲሆን ሲቋቋም የተሟላ ወይም በከፊል የመንግሥት ድጋፍ አገልግሎት ያገኘ ነው፤

7/ "የእፎይታ ጊዜ" ማለት በአዲስ ሕጋዊ ሰውነት አግኝቶ የተዘዋዋሪ ብድር ተጠቃሚ በመሆን ወደሥራ ለሚገባ አዲስ ኢንተርፕራይዝ የምርት ወይም አገልግሎት ወደ ገበያ ለማቅረብ የሚያስፈልገውን የመዘጋጃ ጊዜ ማለትም የቢዝነስ ማስጀመሪያና የመሥሪያ ማሽነሪዎች፣ ጥሬ እቃና የሰው ኃይል ማቅረቢያ ጊዜን ግምት ውስጥ በማስገባት ብድር የማይመለስበት ጊዜ ነው፤

8/ "የግል ኢንተርፕራይዝ" ማለት አንድ የኢንተርፕራይዝ ባለቤት የሚያቋቁመውና የንግድ ባለቤት ያለው ሆኖ የኢንተርፕራይዙ አጠቃላይ እንቅስቃሴና ሥራ በራሱ አቅምና ፍላጎት የተወሰነ ነው፤

9/ "የኅብረት ሽርክና ማኅበር" ማለት ሕጋዊ ህልውና ያለው ሁለትና በላይ በመሆን በውስጠ-ደንቡ መሠረት የመነሻ ካፒታሉ በአባላቱ የጋራ መዋጮ ወይም ሼር ላይ የሚመሠረት ኢንተርፕራይዝ (የንግድ ማኅበር) ነው፤

10/"ምሩቅ ሥራ ፈላጊ" ማለት በመንግሥትና በግል ዩኒቨርሲቲ በዲግሪና በላይ፣ በመንግሥትና በግል የቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ከደረጃ 1 እስከ 5 የተመረቀና የመሥራት ፍላጎትና ችሎታ ያለው የራሱን ሥራ በመፍጠርም ሆነ በመቀጠር ቋሚ ሥራ የሌለው የክልላችን ነዋሪ ነው፤



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የሕግ ምክር ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

11/“በነባር ኢንተርፕራይዝ የተፈጠረ የሥራ እድል” ማለት ነባር ኢንተርፕራይዞች ከዚህ በፊት የሥራ እድል ፈጠርንላቸው ያሉትንም ሆነ ለወደፊቱ የሥራ እድል ለመፍጠር በቢዝነስ ፕላናቸው ያስቀመጡትን ከሥራና ስልጠና ጽ/ቤት ወይም ከአንድ ማዕከላት በሕጋዊ ደብዳቤ ጠይቀው በተቋሙ በኩል ተለይተውና ተገቢውን ስልጠና አግኝተው ተቀጥረው ሥራ ላይ ያሉ ወይም ለቀጣዩም በአዲስ የሥራ እድል ለመፍጠር የተስማሙባቸውን የሥራ እድሎች ይጨምራል፤

12/“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

13/በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር አስተዳደር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

# ክፍል ሁለት

# የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር አስተዳደር አሠራር

## 4. የተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር ተጠቃሚ አዲስና ነባር ኢንተርፕራይዞች የግንዛቤ ፈጠራ፣ ምልመላ፣ ስልጠና እና ማደራጀትን በተመለከተ

1/ በአዲስ ኢንተርፕራይዝ ለመደራጀት የሚመለመለው ወጣት በቀበሌው ወይም በክፍለ-ከተማው ወይም በአንድ ማዕከል አገልግሎቱ የሥራ ፈላጊዎች መዝገብ ላይ የተመዘገበ መሆን አለበት፣ ይህን ባንኩን ወክሎ የሚሳተፈው ሠራተኛም ጭምር ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

2/ በአዲስ ወደ ሥራ የሚገባው ወጣት የብድሩ ተጠቃሚ የሚሆነው ዕድሜው ከ18 እስከ 34 ባለው ክልል የሚገኝ ብቻ መሆን ይኖርበታል፤

3/ የብድር ተጠቃሚ የሚሆኑ ነባር ኢንተርፕራይዞች ከላይ የተቀመጠው የእድሜ ክልል አይመለከታቸውም።

4/ የሚመለመለው የኢንተርፕራይዙ አባል ወጣት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምርምር፣ ማርቀቅና ማጠናቀር ዳይሬክቶሬት

ሀ)የደባል ሱስ ተጠቂ ያልሆነ፣

ለ) ከመጥፎ ሥነ-ምግባር የተላቀቀ፣

ሐ) በሀገሪቱ ሕግ ትርጉም የመሥራት አቅምና ችሎታ ያለው መሆን አለበት፤

5/ በኢንተርፕራይዝ በመደራጀት የተዘዋዋሪ ብድር ተጠቃሚ የሚሆን ወጣት አመለካከትን በተመለከተ በተለይም የግለሰቡን ባህሪ፣ ለሥራው ያለው ዝግጁነትና ፍላጎት፣ በብድሩ ላይ ያለውን ግንዛቤ እና ብድሩን ለመመለስ ያለውን ዝንባሌ በአንድ ማዕከል አገልግሎት በኩል የባለድርሻ አካላት በጋራ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፤

6/ የተመለመለው ወጣት የንግድ ሥራ አመራር ወይም የኢንተርፕርነርሽፕ ስልጠና መውሰድ ይኖርበታል፤

7/ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞቹ በአቅራቢያቸው በሚገኝ የገጠር ቀበሌዎች ወይም የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ (One Stop Center Service) አማካኝነት አስፈላጊውን የግንዛቤ፣ የምዝገባ፣ የአደረጃጀት ድጋፍ፣ እና ዕገዛ ያገኙ መሆን ይገባቸዋል፤

8/ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞቹ በግል ወይም በኅብረት ሽርክና ማኅበር የተደራጁ መሆን ይኖርባቸዋል፤

9/ ወጣቶቹ ሲደራጁ በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሆኖ በተቻለ መጠን የሚተዋወቁ እና በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሆነው ሥራ የሌላቸው መሆን አለባቸው፤

10/ በወጣቶች የተቋቋሙት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አዋጪ የሆነ የሥራ ዕቅድ ያላቸው እና የንግድ እቅዱም በአደራጁና በባንኩ አዋጭነቱ መረጋገጥ አለበት፤

11/ ብድሩ ለሥራ እንጂ ለሌላ ጉዳይ እንደማይውል የተገነዘቡ፣ መመለስ ያለበት መሆኑን ለተረዱና ለሥራ ዝግጁ ለሆኑት ብቻ ይሰጣል፤

12/ ሙያዊ ክህሎት በሚጠይቁ ሥራዎች የሚሰማሩ ወጣቶች ሥራውን ሊያሠራ የሚችል ቴክኒካል ስልጠና መውሰድ ይኖርባቸዋል፤

13/ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚደራጁ ወጣቶች ከዚህ ቀደም በአብቁተ ወይም ጸደይ ባንክ ተበዳሪ ከነበሩ ብድራቸውን ሙሉ በሙሉ የመለሱ፣ የተበላሸና ውዝፍ ዕዳ የሌለባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፤



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ * The ANRS Bureau of Justice *

14/ የብድሩ ተጠቃሚ የሚሆኑ ወጣቶች የመሥሪያ ቦታ በመንግሥት በኩል፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በአካባቢው ማኅበረሰብ፣ በወላጆች ወይም በራሳቸው አቅም ያዘጋጁ መሆኑንና የተዘጋጀው የመሥሪያ ቦታ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ-ልማቶች በተለይም እንደአስፈላጊነቱ መብራት፣ ውሀ፣ መንገድ የመሳሰሉት የተሟሉለት መሆኑን ማረጋገጥ እና በኪራይ የሚቀርቡ የመሥሪያ ቦታዎች ቢያንስ ብድሩ በተበዳሪው እጅ የሚቆይበትን ወይም የብድር ጊዜውን ታሳቢ ያደረገ ሕጋዊ የኪራይ ውል ያላቸው መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፤

15/ ኢንተርፕራይዞቹ የብድሩ ተጠቃሚ ለመሆን ለሥራው የሚያስፈልገውንና ለመበደር የሚጠይቁትን ገንዘብ ቢያንስ 10% /አስር በመቶ/ በአንድ ጊዜ ወይም በሂደት (ብድሩ ከመሰጠቱ በፊት) በቅድመ-ብድር ቁጠባ መልክ ብድሩን ከሚወስዱበት የባንኩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት መቆጠብ ይኖርባቸዋል፤

16/ ነባር ኢንተርፕራይዞች በድጋሚ ብድር ለመውሰድ አሁን ሥራ ላይ ባለው የሥራ ዘርፋቸው ማስፋፊያ ላይ ወይም በጠየቁት ብድር አጠቃቀም አዲስ አዋጪ የሆነ የንግድ ሥራ አመራር እቅድ (ቢዝነስ ፕላን) ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፤

17/ በራሳቸው ካፒታል ወይም በቤተሰቦቻቸው ድጋፍ ወደ ሥራ የገቡ ወይም ከዚህ በፊት የተዘዋዋሪ ብድር ተበድረው የመለሱ ነባር ኢንተርፕራይዞች ለሥራ ፈላጊ ወጣቶች የሥራ ዕድል የፈጠሩ፣ በእድገት ተኮር እና አዋጭነቱን በማረጋገጥ ከተሸከርካሪ ውጪ ባሉ የአገልግሎት ዘርፎች የተሰማሩ፣ በንግድ ሥራ አፈፃጸማቸው የተሻለ እንቅስቃሴ ውስጥ ያሉ እና ብድር ለማግኘት ባቀረቡት ቢዝነስ ፕላን ቢያንስ ተጨማሪ ሁለት ሥራ ፈላጊዎችን ቀጥሮ ለማሠራት በቢዝነስ ፕላናቸው አካተው ያቀረቡ መሆን ይኖርባቸዋል፤

18/ ከሚሰጠው ብድር ውስጥ በአዲስ ሥራ ለሚጀምሩ ኢንተርፕራይዞች 60%ቱን ለነባር ኢንተርፕራይዞች ደግሞ 40%ቱን የሚሸፍን መሆን አለበት፤

19/ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የሚደራጁ ወጣቶች ለሚወስዱት ብድር የአንድነት እና የነጠላ ዋስትና ይገባሉ፣ ለዚህም በቂ ዋስትና ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፤



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ
The ANRS Bureau of Justice
የህግ ምርምር፣ ማርቀቅና ማሠራጫ ዳይሬክቶሬት

20/ ወጣቶቹ ከላይ በተገለፁት መስፈርቶች ከተመለመሉና በግል ወይም በሽርክና ማኅበር ከተደራጁ በኋላ በብድሩ አሠራርና በሚጠበቅባቸው ኃላፊነት ዙሪያ በባንኩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት ስልጠና ይሰጣል፤

21/ በኢንተርፕራይዝ የሚደራጁ ወጣቶች ሲመለመሉ፡-

ሀ) መስፈርቱን ለሚያሟሉ ሴቶችና ለአካል ጉዳተኞች ቅድሚያ ይሰጣል፣

ለ) የሴቶችን ተሳትፎ የበለጠ ከማስጠበቅ አኳያ በግልም ሆነ በቡድን በሚደራጁ ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ቢያንስ 35 በመቶ ሴቶች እንዲሆኑ ይደረጋል፣

ሐ) ተመሳሳይ ፆታና የአካል ጉዳት ሁኔታ ላላቸው ምሩቃን ቅድሚያ ይሰጣል፤

22/ ለመጀመሪያ ዙር ብድር ለመውሰድ የተመለመሉ ወጣቶች ስም ዝርዝርና በተቻለ መጠን ፎቶግራፋቸው ጭምር ብድር ከመውሰዳቸው በፊት ሌሎች ማስረጃዎችን እያሟሉ ጎን ለጎን በተመለመሉበት ቀበሌ ወይም የአንድ ማዕከል አገልግሎት ወይም የቢሮው መዋቅር እና የባንኩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ለህዝብ እይታ አመቺ በሆነ ቦታ ቢያንስ ለ3 የሥራ ቀናት መለጠፍ አለበት፡፡ የወጣቱን ስም ዝርዝርና ፎቶ በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ሳይለጥፉ ብድር መስጠት አይፈቀድም፤

23/ ከመንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሥራ ለቀው ወይም ከመደበኛ ንግድ ሥራ ፈቃድ በመመለስ በጥቃቅን እና አነስተኛ በመደራጀት የተዘዋዋሪ ብድር ተጠቃሚ መሆን አይችሉም፤

24/ በአንድ ኢንተርፕራይዝ በተለያየ ምክንያት አባላት ቢቀንሱ የኢንተርፕራይዙ ህልውና ሊቀጥል ይችላል፣ ከአባልነት በፍቃደኝነት ወይም ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ የሚወጣ አባል ካለ ትርፍና ኪሳራው ከተሠራና የሚወጣው አባል ወይም ወራሽ የሚደርስበትን ብድር አጠቃሎ ለባንኩ በመክፈል ከአባልነት እስከተሰናበተ ድረስ በቀሪው ጊዜ በቀሪ የማኅበሩ አባላት እዳ ሊጠየቅ አይችልም፤

25/ ተበዳሪ ኢንተርፕራይዞች በየደረጃው ያለው የሥራ እድል ፈጠራ ግብረ-ኃይል ካላመነበት በስተቀር ብድሩን የተበደሩበትን የሥራ ዘርፍ መቀየር አይችሉም፡፡

## 5. ተበዳሪ ኢንተርፕራይዝ ማቅረብ ያለበት ማስረጃዎች

1/ የኢንተርፕራይዙ አባላት በተበዳሪዎች የምልመላ ቅጽ ወይም ቃለ-ጉባዔ በሥራ ፈላጊ መዝገቡ ላይ የተመዘገበበትን ተራ ቁጥር ጨምሮ በመጥቀስ መቅረብ ይኖርበታል፤

2/ የተዘዋዋሪ ብድር መጠየቂያ ማመልከቻ ባንኩ በሚያዘጋጀው ቅፅ ተሞልቶ የሚቀርብ ይሆናል፤



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice

3/ የኢንተርፕራይዙን አባላት ማንነት የሚያስረዳ የቀበሌ መታወቂያ ደብተር ከዋናው ጋር የተገናዘበ ፎቶ ኮፒ ተያይዞ ይቀርባል፤

4/ ለሽርክና ማኅበር በሰነዶች እና ጠበቆች ምዝገባ እና ማረጋገጫ የጸደቀ የመተዳደሪያ ደንብ፤

5/ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር (TIN No.)፤

6/ የፀደቀ የንግድ ሥራ ፈቃድ እና የንግድ ስም ስያሜ፤

7/ የመሥሪያ ቦታ ማረጋገጫ (የኪራይ ውል ወይም በአደራጁ አካል ወይም ከቤተሰብ የተሰጠ)፤

8/ የአዋጭነት የንግድ ሥራ እቅድ፤

9/ የንግድ ሥራ አመራር እና የኢንተርፕርነርሽፕ ስልጠና ስለመውሰዳቸው ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት፤

10/ የኢንተርፕራይዙ አባላት ሥራ አስኪያጁ ማኅበሩን ወክሎ የብድሩን ሂደት እንዲያስፈፅም ጠቅላላ ጉባዔው በስም ጠቅሶ ሥራ አስኪያጁን የወከለበት ኢንተርፕራይዙ የሚጠይቀውን የገንዘብ መጠን የያዘ፣ አባላት የፈረሙበት ቃለ-ጉባዔ እና የማኅበሩ ማህተም ያለበት ሆኖ የማኅበሩን አባላት ስምና አድራሻ የያዘ ሰነድ፤

11/ ለሚያስፈልጋቸው የሥራ መስኮች የቴክኒክ ስልጠና እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት።

## 6. ቁጠባን በተመለከተ

1/ ኢንተርፕራይዞች ብድር በሚወስዱበት የባንኩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የፈቃደኛ ቁጠባ ሒሳብ መክፈት ይጠበቅባቸዋል፤

2/ በዚህ የቁጠባ ሒሳብ ለሚሰማሩበት የሥራ መስክ የሚያስፈልገውን የብድር መጠን ቢያንስ 10% /አስር በመቶ/ በአንድ ጊዜ ወይም በሂደት (ከብድር በፊት) በቅድመ ብድር ቁጠባ መልክ መቆጠብ ይኖርባቸዋል፣ ይህ የቅድመ-ብድር ቁጠባም የብድሩ አካል (Matching fund) ሆኖ ኢንተርፕራይዙ የሚጠቀምበት ይሆናል፤

3/ ኢንተርፕራይዙ ከሚያገኘው ገቢ በተከታታይ ቁጠባ እንዲቆጥብ ይበረታታል፣ ተበዳሪ ኢንተርፕራይዙ የተበደረውንና በድህረ-ብድር ቁጠባ የቆጠበውን ገንዘብ ለሥራ እየፈለገው በባንኩ በኩል ለቁጠባ በሚል መያዝ አይቻልም፤



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice

4/ የኢንተርፕራይዝ አባላት እና በኢንተርፕራይዙ ውስጥ የሥራ ዕድል የሚፈጠርላቸው ዜጎች በየራሳቸው የቁጠባ ሂሳብ በመክፈት በየጊዜው ከሚያገኙት ገቢ እንዲቆጥቡ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

## 7. የኢንተርፕራይዞች የሥራ መስክ

1/ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ትርፍ በሚያስገኙ ዕድገት ተኮር ዘርፍ እና ከተሽከርካሪ ውጪ በሆኑ አዋጪነታቸው በተረጋገጠ የአገልግሎት ዘርፎች፣ ረዘም ያለ ቅድመ-ዝግጅት ሳያስፈልግ ወደ ሥራ በሚያስገቡ የሥራ ዘርፎች መሰማራት አለባቸው፤

2/ ኢንተርፕራይዞች የሚያቀርቧቸው ፕሮጀክቶች ወይም የሥራ ዕቅዶች በቀላሉ ሊተገበሩ የሚችሉ አዋጭ እና አካባቢ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሌላቸው፤ ግብአት በቀላሉ ሊያገኙ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## 8. የብድር ስርጭትና መጠንን በተመለከተ

1/ ማነኛውም ወረዳ ወይም ከተማ ወይም ክፍለ-ከተማ ከዚህ በፊት ተሰራጭቶ ከነበረው ተዘዋዋሪ ብድር የተመለሰና የተቀመጠ እና ለወደፊትም የሚኖር የወጣቶች የተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር በክልሉ በሁሉም አካባቢ በሚገኝ የባንኩ ቅርንጫፍ 97% እና በላይ የሚለው የብድር አመላለስ ምጣኔ ሳይገድበው ማሰራጨት ይችላል፤

2/ በወረዳው ወይም በከተማ አስተዳደሩ ስር የሚገኙ የባንኩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የሚያሰራጩት የብድር ገንዘብ መጠን ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደሩ ካለው ተመላሽ ገንዘብ ወይም ከተመደበለት የተዘዋዋሪ ገንዘብ መጠን በላይ መሆን የለበትም፤

3/ በተለያየ ምክንያት ለብድር አገልግሎት መዋል የሚገባውን ገንዘብ እያለ ከ6 ወራት በላይ ምንም አይነት ብድር የማያበድር ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ካለ ገንዘቡ በዞን የሥራ እድል ፈጠራ ግብረ-ኃይል በኩል ከአንድ ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወደ ሌላ ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ሊዛወር ይችላል፣ የዞኑ ሥራ እድል ፈጠራ ግብረ-ኃይል በጀቱን ሲያዘዋውር አስቀድሞ በጀቱ ለሚቀነስበትም ሆነ ለሚጨመርለት ወረዳ እንዲሁም ለባንኩ የግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢ በፈረመበት ደብዳቤ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፣ ይህ የብድር ማዛወር ሥራ በክልሉ የሥራ እድል ፈጠራ ግብረ-ኃይል በኩልም ከዞን ዞን እንዲዛወር ሊደረግ ይችላል፤

4/ ከሌላ ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ያላቸውን ገንዘብ ባለማበደራቸው ምክንያት ተነስቶ የሚዛወርለት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር በእጁ ላይ ያለውን የተመለሰም ሆነ



The ANRS Bureau of Justice

የተበጀተ የተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር ሙሉ በሙሉ ያበደረና የብድር አመላለስ ምጣኔው ከ97 ፐርሰንት እና በላይ የሆነ መሆን አለበት፤

5/ ኢንተርፕራይዞች የሚወስዱት የብድር መጠን እንደሚሰማሩበት የሥራ ዘርፍ እና ደረጃ የሚለያይ ቢሆንም ለአንድ ኢንተርፕራይዝ ሊፈቀድ የሚችለው ከፍተኛው የብድር መጠን፦

ሀ) ለግል ኢንተርፕራይዝ እስከ ብር 250,000 (ሁለት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) ሲሆን የኢንተርፕራይዙ አባላት ቁጥር አምስት እና ከዚያ በላይ ከሆነ እስከ 1,250,000 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) ሊደርስ ይችላል፣

ለ) ከሁለት እስከ አራት አባላት ያለው ኢንተርፕራይዝ የብድር መጠን ከፍተኛው የብድር ጣራ የብድሩ መጠኑ ለአባላቱ ብዛት ሲካፈል ለግል ኢንተርፕራይዝ ከሚሰጠው ብድር በላይ ሊሆን አይችልም፣

ሐ) በእራሳቸው መነሻ ገንዘብ ወይም በቤተሰቦቻቸው ድጋፍ ሥራ ላይ ላሉ ኢንተርፕራይዞች ወይም የተዘዋዋሪ ብድር ወስደው ለመለሱ ኢንተርፕራይዞች ለአንድ ግለሰብ እስከ ብር 250,000 (ሁለት መቶ ሀምሳ ሺ ብር ሲሆን የአባላቱ ቁጥር አምስት እና ከዚያ በላይ ከሆነ እስከ 1,250,000 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) ሊደርስ ይችላል፡፡

6/ ነባር ኢንተርፕራይዞች የብድር ተጠቃሚ የሚሆኑት ሌሎች መስፈርቶችን ማሟላታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚስተናገዱበት ቅደም ተከተል ማሟላት የሚገባቸውን አሟልተው በማመልከቻ በጠየቁበት ቅደም ተከተል ሆኖ ከዚህ በፊት የተዘዋዋሪ ብድር ተጠቃሚ የነበሩ ኢንተርፕራይዞች መካከል ግን ከዚህ በፊት የተበደሩትን ብድር በውል ስምምነታቸው በተስማሙበት የጊዜ ገደብ የከፈሉ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ሆኖ እያቀራረጡ ሲከፍሉ የነበሩ ወይም በፍርድ ቤት ክስ ተመሥርቶባቸው ውሳኔ ሳይሰጥ ክሱን አቋርጠው ብድራቸውን ሙሉ በሙሉ የከፈሉ ተከታይ ሆነው ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፤

## 9. የብድር ማፅደቅ ሂደት

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የተገለፁ ዝርዝር መስፈርቶችን ያሟሉ ኢንተርፕራይዞች የብድር ጥያቄ በአቅራቢያው ባሉ የባንኩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከደረሰ በኋላ መስፈርቶቹ መሟላታቸውን በማረጋገጥ በተቀመጠው አሠራር መሠረት ተገቢው የትንተናና የብድር ማፅደቅ ሥራ መከናወን አለበት፤

2/ መስፈርቱን አሟልቶ የተገኘ የብድር ጥያቄ በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ደረጃ 3 ተከታታይ የሥራ ቀናት፣ በዞን ደረጃ 5 ተከታታይ የሥራ ቀናት፣ በክልል ደረጃ 7 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ብድሩ ጸድቆ ለተበዳሪዎች መተላለፍ አለበት።

## 10. የተዘዋዋሪ ብድር ዋስትናን በተመለከተ

1/ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የወሰዱት ብድር ለካፒታል ዕቃዎች ወይም ቋሚ ዕቃዎች መግዥያ ከሆነ በብድር የተገዙ ዕቃዎች በዋስትናነት ሊያዙ ይችላሉ፤

2/ ሁሉም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አባላት ለሚወስዱት ብድር የአንድነት እና የነጠላ ዋስትና መፈረም ይኖርባቸዋል፤

3/ ተበዳሪዎች በመመሪያው በተቀመጠው የዋስትና ሥርዓት መሠረት ዋስትና ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፣ የሚቀርቡ የዋስትና ዓይነቶችም፡-

ሀ) የከተማ ካርታና ፕላን ያለው ቤት፣

ለ) የቋሚ ሠራተኛ ደመወዝ፣

ሐ) የ2ኛ ደረጃ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፣

መ) ተሽከርካሪ፣

ሠ) ሌሎች ተንቀሳቃሽ ንብረቶች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው የአፈጻፀም መመሪያ መሠረት ተግባራዊ ይደረጋል፤

4/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተመለከተው መሠረት ለዋስትና የሚያዘውን ንብረት ግምት በባንኩ መደበኛ አሠራር አግባብ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 11. የተዘዋዋሪ ብድር ወለድ

አዲስም ሆኑ ነባር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በሚወስዱት ብድር ላይ የሚከፍሉት የወለድ መጠን 8 በመቶ ብቻ ነው።

## 12. ተዘዋዋሪ ብድር ስለመስጠት ወይም ስለመልቀቅ

1/ ብድር የፀደቀላቸው ኢንተርፕራይዞች የብድር እና የዋስትና ውል ስምምነት መፈረም ይኖርባቸዋል፤

2/ ለኢንተርፕራይዙ የተፈቀደው የብድር መጠን አስቀድሞ በኢንተርፕራይዙ ስም ወደ ተከፈተው የቁጠባ ሂሳብ ይተላለፋል፤

3/ ኢንተርፕራይዞች የተፈቀደላቸውን ገንዘብ ብክነት ለመታደግ የወረዳና የከተማ ጽሕፈት ቤት፣ የቀበሌና የአንድ ማዕከል አገልግሎት በተለይም በተቻለ መጠን ጥሬ ገንዘብ በኢንተርፕራይዙ እጅ ሆኖ ለብክነት እንዳይጋለጥ ጥብቅ ድጋፍና ክትትል ማድረግ አለባቸው፤

4/ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞቹ የተፈቀደው ብድር ለካፒታል ወይም ለቋሚ ዕቃ መግዣ ከሆነ ኢንተርፕራይዙ በሚያቀርበው ዋጋ ማቅረቢያና የቁጠባ ወጪ ጥያቄ መሠረት ከቁጠባ ሂሳቡ ወጪ በማድረግ ለአቅራቢዎች የሚከፈል ይሆናል፣ ይህንንም በጽሕፈት ቤት ደረጃ ያሉ አካላት ክትትል በማድረግ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፤

5/ በተሰጠው የብድር ውሳኔ መሠረት ለሥራ የተፈቀደው ብድር ከኢንተርፕራይዙ ጋር የሥራ ውል ለሚኖራቸው አቅራቢዎች፣ የሥራ ተቋራጮች፣ ለአገልግሎት ሰጪዎች እና ይህን መሰል ግንኙነት ላላቸው አካላት የተሟላ ሰነድ ሲቀርብ ከቁጠባ ሂሳባቸው ወጪ በማድረግ በቀጥታ እንዲከፍሉ ይደረጋል፤

6/ የባንኩ ቅርንጫፉ በሚያቀርበውና በሥራ እድል ፈጠራ ግብረ-ኃይሉ ተገምግሞ የተረጋገጠውን ተሰራጭቶ ያልተመለሰ የተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር ከወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር በጀት ላይ በጀት በሚመደብበት ወቅት እንዲቆረጥ ይደረጋል፤

7/ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ከተሰጠው ብድር ውስጥ እስካሁን ያልተመለሰ እና ወደፊትም የማይመለስ ካለ በዝርዝር መረጃ ከነምክንያቱ ለወረዳው ወይም ለከተማው ግብረ-ኃይል ሪፖርት ያደርጋል።

## 13. የተዘዋዋሪ ብድር መክፈያ ጊዜ

1/ ለአዲስ ኢንተርፕራይዞች የሚወስዱት ብድር የመክፈያ ጊዜ እንደተሰማሩበት የሥራ መስክ እና እንደወሰዱት የብድር መጠን የሚለያይ ሆኖ ዝቅተኛው የእፎይታ ጊዜ 3 ወር ይሆናል፤

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice

2/ ከ3 ወር በላይ ለኢንተርፕራይዞቹ የሚሰጠው የእፎይታ ጊዜ እንደተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ እና የብድር አይነት እየታየ የሚወሰን ይሆናል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑሥ አንቀጽ 1 እና 2 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ነባር ኢንተርፕራይዞች የብድር እፎይታ ጊዜ አይሰጣቸውም፤

4/ የብድር አመላለሱ የሚሰጥ የእፎይታ ጊዜ ሲጠናቀቅ አጠቃላይ የብድር ቆይታ ወራት የሚባለው የእፎይታ ወራትን በመቀንስ ለሚቀረው የብድር ወራት በሚደረግ ስሌት የሚገኘውን ወርሃዊ የብድር ተመላሽ መጠን እንዲከፈል ይደረጋል፤

5/ የእፎይታ ጊዜው ተደራርቦ በአንድ ጊዜ እንዳይከፈል በየሥራ ዘርፎቹ የእፎይታ ጊዜ በባንኩ አቅራቢነት ይህን መመሪያ ለማስፈጸም የውል ስምምነት የተፈራረሙ ተቋማት የሚስማሙበት አሠራር ሆኖ እንዲተገበር ይደረጋል፤

6/ የብድር መመለሻ ጊዜው እንደየሥራ ባህሪው ታይቶ ማጠናቀቂያ ጊዜው ከአምስት /5/ ዓመት እንዳይበልጥ ሆኖ የሥራ ዘርፎቹና የብድር የቆይታ ጊዚያቸው ይህን መመሪያ ለማስፈጸም የውል ስምምነት በተፈራረሙ ተቋማት በየጊዜው እየታየና እየጸደቀ በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች እንዲፈጸም ይደረጋል፤

7/ የብድር ክፍያውም እንደ ሥራ መስኩ የገንዘብ ፍሰት ባህሪ በብድር ማፅደቅ ሂደቱ ላይ እየተመዘነ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩ፣ በየዓመቱ የሚፈፀም ሆኖ የተጠቀሰው የብድር መክፈያ ጊዜ በየሥራ ዘርፎቹ ለማስቀመጥ በባንኩ አቅራቢነት ከሌሎች ይህን መመሪያ ለማስፈጸም የውል ስምምነት ከሚወስዱ ተቋማት ጋር በየጊዜው ታይቶ እየጸደቀ እንዲወርድ ይደረጋል፤

8/ የብድር ማስመለስ ሂደቱ ወለድ ቅድሚያ የሚሰበሰብበት ሳይሆን በአለም አቀፍ የብድር አመላለስ ስሌት አግባብ ከዋናው ወይም ከአይነቱም ሆነ ከወለዱ በስሌቱ አግባብ ተፈጻሚ ሆኖ በየወሩ የሚመለሰው የብድር መጠን ከዋናው የሚመለሰው እየጨመረ፣ ወለዱ እየቀነሰ በወርሀዊ ክፍያው ላይ ምንም አይነት ልዩነት ሳይኖረው ተፈጻሚ ይሆናል።

## 14. ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት

በሃይማኖታዊ ምክንያቶች ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሚከተሉት አማራጮች መጠቀም ይቻላል፡-

1/ አማራጭ 1 ለሚሰጣቸው ብድር የሚከፍሉት የአገልግሎት ክፍያ ወይንም ኮሚሽን ቅድሚያ በመሰብሰብ ወይም እንዲከፍሉ በማድረግ የሚፈፀም ሆኖ የአገልግሎት ክፍያ ወይም ኮሚሽን መጠኑ 8% ይሆናል፤

2/ አማራጭ 2 ኮሚሽኑ እንደ ብድሩ የአመላለስ ባህሪ አስቀድሞ ተሰልቶ ከዋናው ብድር ጋር ተጨምሮ ውል ላይ ተካቶ ተይዞ እንዲመለስ ይደረጋል፤

3/ አማራጭ 3 ኮሚሽኑ እንደ ብድሩ የአመላለስ ባህሪ አስቀድሞ ተሰልቶ ከዋናው ብድር ጋር ተጨምሮ ውል ላይ በማካተትና ተበዳሪዎች ከገንዘቡ ጋር ሳይነካኩ በአይነት ተገዝቶ እንዲወስዱና እቃው የተገዛበት በውል የተያዘውን ገንዘብ ወይም የእቃው ወይም ዓይነቱ ዋጋ ተብሎ ውል የተወሰደበትን ለመመለስ በተወሰደው ስምምነት ለወሩ አካፍሎ በየወሩ እንዲመልሱ ይደረጋል፡፡

## 15. ድህረ-ብድር ተግባራት

1/ በቀበሌ ወይም በአንድ ማዕከል አገልግሎት ወይም በጽሕፈት ቤት ደረጃ ያሉ ፈፃሚ አካላት ኢንተርፐራይዞች ብድር ከተሰጣቸው በኋላ ከ15 እስከ 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ እና በየወሩ በተከታታይ በሥራ ቦታቸው በአካል በመገኘት የብድር አጠቃቀማቸውን መገምገምና ማረጋገጥ ይገባቸዋል፤

2/ ለኢንተርፐራይዞች ውጤታማነት አስቀድሞ በተዘጋጀ ፕሮግራም መሠረት ቀጣይነት ያለው አካላዊ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፤

3/ በየጊዜው በሚደረገው ድጋፍ በየኢንተርፐራይዙ የሚለዩ ክፍተቶች በስልጠና እንዲሞሉ መደረግ ይኖርበታል፤

4/ የኢንተርፐራይዞቹን ዘላቂነትና ምርታማነት ለማሳደግ ተከታታይነት ያለውና ጥራቱን የጠበቀ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ይገባዋል፤

5/ የሥራ አፈፃፀማቸው በገበያ ችግር እንዳይስናከል አስቀድሞ በተገቢው በተጠኑ ሥራዎች እንዲሰማሩ የሚደረግ ሲሆን በሂደት በሚያጋጥሙ የገበያ ችግሮች የገበያ ትስስር ሥርዓት መዘርጋት ይጠበቃል፡፡

## 16. ተዘዋዋሪ ብድር ማስመለስ

1/ የባለድርሻ አካላት ዋና ተግባር ኢንተርፕራይዞቹ ብድር ከመውሰዳቸው በፊት ብድሩን በተመለከተ ገንዘቡን እንደ እርዳታ የመመልከት፣ ወለድን ጨምሮ ዋናውን ገንዘብ ተመላሽ ያለማድረግ ችግርን ለመቅረፍ ጥልቅ ግንዛቤ እና የጠራ አመለካከት እንዲኖራቸው ማድረግ ይሆናል፤

2/ የተዘዋዋሪ ብድር ማስመለሱም ተግባር የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ትኩረት የሚጠይቅ ሆኖ ውጤታማ ሳይሆን ቢቀር ተዘዋዋሪ ፈንዱ የመላው የአማራ ወጣቶች ሀብት ቢሆንም በወሰደው የኮሚሽን ስምምነት መሠረት የብድር ማስራጨትና ማስመለስ ኃላፊነት የባንኩ ይሆናል፤

3/ ሀብትነቱ የክልሉ ህዝብ በተለይም የወጣቱ ሀብት በመሆኑ በየደረጃው የሚገኙ የፍትሕ አካላት ብድሩን በማስመለስ ሂደት በባለቤትነት ይሳተፋሉ፤

4/ ባልተመለሱ ብድሮች ላይ ለሚፈጠር ክስ ባንኩ ጠበቃ አቁሞ መከራከሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ዓቃቤ-ሕግ ብድሩ ባለመመለሱ የወረዳው ወይም የከተማ አሥተዳደሩ ለባንኩ የከፈለውን የመንግሥትና የህዝብ ሀብትን ለማስመለስ መንግሥትን ወክሎ ይከራከራል፤

5/ በየደረጃው ያለ የሥራ እድል ፈጠራ ግብረ-ኃይል ከሚለካባቸው ተግባራት አንዱ የብድር ማስመለስ በመሆኑ በባለቤትነት የሚፈጽሙት መሆን አለበት።

## 17. መረጃ አያያዝና የሪፖርት ግንኙነት

1/ ከቀበሌ ወይም ከአንድ ማዕከል አገልግሎት ጀምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ከባንኩ ጋር በመገናኘት በተዘዋዋሪ ፈንዱ ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞችንና አባሎቻቸውን በሚመለከት ተመሳሳይና ወጥነት ያለው መረጃ ሊይዙ ይገባል፤

2/ የተዘዋዋሪ ብድር የወሰዱ ኢንተርፕራይዞችና አንቀሳቃሾች መረጃ በየተቋማቱ መዋቅራዊ አደረጃጀት በተመሳሳይ ይዘት መያዝ ይኖርበታል፤

3/ በባንኩ መዋቅርም ብድር ያገኙ ኢንተርፕራይዞች በስም ዝርዝር በየሳምንቱ በገጠር እና በከተማ ተለይቶ መላክ ይኖርበታል፣ በየወሩም የብድር ስርጭትና አመላለስ ያለበትን ሁኔታ ለቢሮው የተጠቃለለ ሪፖርት መላክ ይገባዋል፤

4/ የመረጃ አያያዙም የገጠርና የከተማ ተለይቶ በጥንቃቄ መመዝገብ ይኖርበታል።

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የተሰራጨ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር በነበረው አሠራር የሚስተናገድ ይሆናል።

### 19. የተሻሩ ሕጎች

1/ የወጣቶችን ፈንድ ለማስተዳደር በቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዝ ቢሮ ታሕሳስ 2011 ዓ.ም የወጣው መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

2/ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ ልማዳዊ አሰራር እና ሰርኩላር ደብዳቤ ተፈጻሚነት የለውም።

### 20. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

1. ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት ከጸደቀበት ሰኔ 29/ 2014 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ አዲስ ቁጥር ከተሰጠው በኃላ የሚቋቋም መብት ወይም ግዴታ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በአስተዳደር ተቋሙ ድረገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

ባሕር ዳር

ሰኔ 29/2014 ዓ.ም

ይልቃል ከፋለ (ዶ/ር)

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዚዳንት



የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ የህግ ምርምር፣ ማርቀቅና ማሰራጨት ዳይሬክቶሬት The ANRS Bureau of Justice